# ተደብቆ ስለሚቆይ ሳምባነቀርሳ (TB) ኢፌክሽን መድሀኒትዎ ሊያውቁት የሚያስፈልግ ነገር

## RIFAMPIN

ተደብቆ የሚቆይ TB ኢንፌክሽንዎትን ለማከም ይሆን ዘንድ መድሀኒት ተሰጥዎታል። TB የሌለብዎ ሲሆን እርሶ ወደሌሎች TBን ሊያስተላልፉ አይችሉም። ይህ መድሀኒት በ TB በሽታ ከመያዝ  ይከላከልዎታል።

### ይህንን መድሀኒት በመውሰድ ወቅት፡

- የሚያሳስብዎ ነገር ያለ እንደሆነ ለሀኪምዎ ወይም ለነርስዎ ያሳውቁ።
- ወደ ታቀደው የክሊኒክ ጉብኝትዎ ይሂዱ።
- ምንም አይነት የአልኮል መጠጥ የ ሚጠቀሙ አንደሆነ ለሀኪምዎ ያሳውቁ። አልኮል የጎንዮሽ ጉዳት እንዲፈጠር ሊያደርግ ይችላል።
- ለሀኪምዎ ስለሚወስዱት ሌሎች መድኒቶች ያሳውቁ።
- ለሌኛው ሀኪምዎ መድሀኒት እየወሰዱ ያሉት ለተደበቀ የ TB ኢነፌክሽን እንደሆነ ማሳወቅዎትን አርግጠኛ ይሁኑ።
- መድሀኒቶችዎን በሙሉ በሀኪምዎ ወይንም በነርስዎ እንደተነገርዎ ይውሰዱ።
- አንዳንድ ሰዎች መድሀኒቱን ከምግብ ጋር በሚወስዱበት ወቅት መድሀኒቱ የሚፈጥረውን ተጽእኖ እንደሚቀንስላቸው አሳውቀዋል።

### መድሀኒቶችዎን ለመውሰድ እርዳታ የሚያደርጉ አንዳንድ ምክሮች፡

- ✓ መድሀኒትዎን አንድ አይነት ሰአት ላይ በየእለቱ ይውሰዱ።
- ✓ መድሀኒትዎን በሚወስዱበት ሰአት ላይ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ የማንቂያ ደውል ያድርጉ።
- ✓ የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ እንዲያስታውስዎ ይጠይቁ።
- ✓ ፒልቦክስን ይጠቀሙ።
- ✓ በመስታወትዎ ላይ ወይም ማቀዝቀዣዎ ላይ ማስታወሻ እንዲቀመጥ ያድርጉ
- ✓ ቀኑ ላይ ምልክት ያደርጉ ዘንድ የቀን መቁጠሪያ ያስቀምጡ።

### የተደበቀ የ TB ኢንፌክሽን መድሀኒት መርሀግብር፡

(አቅራቢዎች፡ ትክክለኛውን መርሀ ግብር፣ ቀናት እና የኪኒኖች ቁጥር ያመለክታሉ)

| መድሀኒት | መርሀግብር | እለታዊ የኪኒን ቀናት | የጊዜው ርዝመት |
|---|---|---|---|
| Rifampin | በየእለት | | 4 ወራት |

መድሀኒትዎን ይወስዱ ዘንድ ሀኪምዎ ከጤና ባለሞያ ጋር እንዲገናኙ ሊያደርግ ይችላል። ይህም በቀጥታ የሚታይ ህክምና (DOT) በመባል ይታወቃል።

**መድሀኒት መውሰድ የሚረሱ እንደሆነ፡ እለቱ ያው ከሆነ መድሀኒቱን እንዳስታወሱ ወዲያው ይውሰዱ። በአንድ ጊዜ ሁለት መድሀኒት ይውሰዱ።**

| ማስታወሻ |
|---|
| የሀኪሜ ስም፡ |
| የክሊኒኬ ስም፡ |
| የክሊኒኬ ስልክ ቁጥር፡ |




### እነዚህን ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች ይመልከቱ፡

መድሀኒትዎን ወዲያው መውሰድዎትን **ያቁሙ እና** ለ TB ሀኪምዎ ወይም ነርስ በመደወል ምንም አይነት ችግር የሚያጋጥም አንደሆነ ያሳውቁ፡

- ዝቅተኛ የሆነ የምግብ ፍላጎት፣ ወይ ምንም የምግብ ፍላጎት
- የታመመ ሆድ ወይም ቁርጠት
- ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ
- ኮላ - ቀለም ያለው ሽንት ወይም ቀላል ሰገራ
- በቀላሉ መቁሰል ወይም መድማት
- ሽፍታ ወይም ማሳከክ
- የቆዳ ወይም አይን ቢጫ መሆን
- ከፍተኛ ድካም ወይም መዳከም
- ትኩሳት
- የራስ ወይም ሰውነት ህመም
- ማዞር

**ማስታወሻ፡ሽንት፣** ምራቅ ወይ እምባ ቡርትካናማ ቀለም ያለው የሆነ እንደሆነ ምንም አይስጉ። ለስላሳ ኮንታክት ሌንሶችም ቀለማቸው ሊለወጥ ይችላል።

Centers for Disease Control and Prevention Division of Tuberculosis Elimination የተወሰደ መረጃ
SNTC በ Centers for Disease Control and Prevention ፈንድ የሚደረግ ሲሆን በ cooperative agreement #U52PS004089 መሰረት ነው
Published 2017 – Amharic